# ሕይወት ለሰጠ ሞት?

እናት ታምጣለች፡፡ ያለ የሌለ ኃይሏን ሁሉ እያሚጠጠች፡፡ የመንደሯ አዋላጅ እሜቴ ድንበሯ «አይዞሽ ግፊ» ይላሉ እየደጋገሙ፡፡ የመንደሯ ታላላቅ ሴቶችም ዙርያዋን ከብበው «ማርያም ማርያም» እያሉ ይለምናሉ፡፡ አንዳንዶቹ «የመጀመርያዋ ስለሆነ ነው» ይላሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ «ምናልባት ጭንቅላቱ ትልቅ ሆኖ ይሆናል» ይላሉ፡፡ ብቻ ሁሉም በሁላገርሽ ላይ ምጡ የጠና በትን ምክንያት እንደ መሰላቸውን ይተነትናሉ፡፡

ሁላገርሽ መንፈሷም ዐቅሟም እየደከመ መጣ፡፡ ሰውነቷን ላብ አጠመቀው፡፡ ድንገት እንደ ብራቅ እሪ ብላ ስትጮኽ ልጁ ፈትለክ ብሎ ወጣ፡፡ በዚያውም የሁላገርሽ ነፍስም አብራ ወጣች፡፡

እሜቴ ድንበሯ «ኧረ ቀዘቀዘችብኝ፤ ኧረ አንድ በሉኝ» እየተርበተበቱ ጮኹ፡፡ የሚያደርጉት ነገር ግራ ገባቸው፡፡ ሁላገርሽ ቀዝቅዛባቸዋለች፣ ሕፃኑ ደግሞ ብቅ ብሏል፡፡

ይህን ጊዜ ወደዚህች ምድር አዲስ ሆኖ የመጣው ሕፃን አንዳች ፍጡር ከፊት ለፊቱ ቆሞ አየ፡፡ ጥልማሞት የመሰለ አስፈሪ ፍጡር፡፡ ርዝመቱ በመልአክ እንጂ በሰው ክንድ የማይደረስበት፡፡ በዓለም ላይ ያሉ አስቀያሚ ገጽታዎችን ሁሉ ሰብስቦ የያዘ፡፡ በእጁ ደግሞ የሁላገርሽን ነፍስ ይዟታል፡፡

ከሁላገርሽ ማኅፀን የወጣው አዲስ ሕፃን ገና የፍርሃት ስሜት አልተፈጠረበትም፡፡ ስለ ጭራቅ እና ስለ ሰይጣን የሚነገሩ እውነቶችንም ተረቶችንም ገና አልሰማም፡፡ ደግነት እና ክፋት፣ መልካም እና ክፉ ገና በማኅበረሰቡ ደንብ ተለይተው አልተሳሉበትም፡፡ እናም ያንን ጥልምያኮስ የመሰለ ፍጡር አልፈራውም፡፡

«አንተ ማነህ? ደግሞስ የእናቴን ነፍስ የትነው የምትወስዳት?» ሲል ጠየቀው፡፡

«እኔማ ሞት ነኝ፡፡ እናትህ አንተን እወልዳለሁ ብላ ሞተች፡፡ ያንተ ሕይወት ሲጀመር የእርሷ አለቀ፤» ሲል አስቃቂ ጥርሶቹን ብልጭ አደረገበት፡፡

«እንዴት ሕይወት የሚሰጥ ሕይወት ያጣል፡፡ እንዴት ላለው ይጨመርለታል እንጂ ይወሰ ድበታል፤ እንዴት የሚሰጥ ይራባል፤ እንዴትስ የሚያበራ ይጨልምበታል» ሲል ጠየቀው፡፡

«እርሱን እኔ አልመልስልህም፤ የኔ ድርሻ ነፍሷን መውሰድ ብቻ ነው» አለው ሞት፡፡

«ይህ ከሆነማ እኔም እከተልሃለሁ፡፡ ምንጩን የሚያደርቅ ውኃ፣ ፋኖሱን የሚያጠፋ መብራት፣ ማሳውን የሚገደል እሸት፣ ዛፉን የሚገነድስ ፍሬ፣ ምጣዱን የሚሰብር እንጀራ መሆን የምፈልግ ይመስልሃል?» አለው ሕፃኑ፡፡

«እርሷን እንጂ አንተን ለመውሰድ አልመጣሁም» አለው ሞት ከፊቱ እንደ መራቅ እያለ፡፡

«ነገርኩህኮ እኛ ሰዎች እንጂ እፉኝቶች አይደለንም፡፡ የእፉኝት ልጆች ሲፀነሱ አባታቸው፣ ሲወለዱ እናታቸውን ይገድላሉ ይባላል፡፡ እኛ ግን ሰዎች ነን፡፡»

«አንተ ለፈጣሪ የሚጠየቀውን ጥያቄ ነው እኔን የምትጠይቀኝ» አለው ሞት፡፡

«አሁን ገና እውነት ተናገርክ» አለና ሕፃኑ አንገቱን ወደ ሰማይ ቀና አደረገ፡፡ ከዚያም እንዲህ ሲል አሰምቶ ጮኸ፡፡

«ፈጣሪ ሞቷል»

ያን ጊዜ እልፍ አእላፍ መላእክት እንደ እሳት ላንቃ የሚንበለበል ሰይፋቸውን መዝዘው፣ የእሳት ዝናር ታጥቀው በሕፃኑ ዙርያ ቆሙ፡፡

«ምን አልክ?» ሲል አንደኛው መልአክ ጠየቀው፡፡

«ፈጣሪ ሞቷል» አለና ሕፃኑ ላንቃው እስከሚሰነጠቅ ጮኸ፡፡

«ይህ የድፍረት ኃጢአት ነው፤ ከባድ ወንጀልም ነው፡፡ አንተ ገና ዓለምን አላየህም፤ መጻሕፍትን አላነበብክም፣ ከሰዎች ሕይወት አልተማርክም፤ ከራስህም ሕይወት ልምድ አልቀሰምክም፡፡ እንዴት ከጥቂት ሰዓታት በፊት ተወልደህ እንዲህ ያለ ድፍረት ይወጣሃል» ሲል ተናገረው መልአኩ በቁጣ፡፡

«ልክ ነው» አለ ሕፃኑ፡፡ «ልክ ነው የተናገርኩት ድፍረት እንደሆነ፤ እመቀ እመቃት የሚከት ኃጢአት እንደሆነም ዐውቃለሁ» አለ ሕፃኑ በዙርያው የከበቡትን መላእክት በለጋ ዓይኑ እያየ፡፡ «ግን እስኪ ልጠይቃችሁ? ሕይወት የሰጠችኝ እናቴ ከሞተች፣ ለዓለም ሕይወት የሰጠ ፈጣሪ ሞቷል ማለት ነውኮ፡፡ እናቴኮ የፈጣሪን አደራ ተረክባ የፈጣሪን ሥራ ነበር የሠራችው፡፡ ሕይወትን ለሰጠ ዋጋው ሞት ከሆነ ለዓለም ሕይወትን ለሰጠ ፈጣሪ ምን ዋጋ ተከፈለው ታድያ?» ሲል ጠየቃቸው፡፡

በዚህ ጊዜ የብዙዎቹ መላእክት ሰይፎች ቀዘቀዙ፡፡ የአንዳንዶቹም ወደ ሰገባቸው ተመለሱ፡፡ ሌሎች ደግሞ ያንን የሰዓታት ሕፃን በአንክሮ ተመለከቱት፡፡ እንዲህ ያለ ነገር አጋጥሞት የማያ

ውቀው ሞት ግራ ተጋባ፡፡ ጉዳዩ በዚህ እንደማያቆም ገባው መሰል እፍን አድርጎ ይዟት የነበረውን የሁላገርሽን ነፍስ ለቀቅ አደረጋት፡፡

ወዲያው ምድርን ከአፅናፍ እስከ አጽናፍ ያነጋነገ ክስተት ተፈጠረ፡፡

ፀሐይ ጨለመች፡፡ ከዋክብት ረገፉ፡፡ ወንዞች እና ምንጮች ደረቁ፡፡ አየራት ጸጥ አሉ፡፡ ምድር መዞሯን አቋርጣ ቆመች፡፡ በሕፃኑ ዙርያ የቆሙት መላእክት የምጽአት ቀን የመጣ መሰላቸውና ሰይፋቸውን መዘዙ፡፡

ከሰማያት የመጣ ድምጽ ግን ፍጡራንን እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፡፡ «ለምን እንዲህ አደረጋችሁ?»

ፀሐይም ተነሣች፡፡ እንዲህም አለች «እኔ ለዚህ ዓለም ሌት ተቀን ብርሃንን እሰጣለሁ፡፡ እኔ የምሰጠውን ብርሃን የሚቀበል፣ ነገር ግን ብርሃኑን የምሰጠውን እኔን የማይፈልግ ሕግ ካለ ለምን እኖራለሁ?»

ከዋክብቱ «የኛም ጥያቄ ነው» አሉና ብልጭ፣ብልጭ፣ ብልጭልጭ ብለው አጨበጨቡ፡፡

ወንዞችም እንዲህ አሉ፡ «ውኃ የሚሰጥ ወንዝ እንዲደርቅ ከተደረገ የኛ መኖርስ ለምንድን ነው?»

ምንጮችም «ይህ የኛም ጥያቄ ነው» አሉና ፏፏቴ አሰሙ፡፡

አየራትም አሉ «የኛን አየር እየተነፈሱ እኛን የሚበክሉን ከሆነ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ መኖር አንፈልግም»ከአራቱ መዓዝናት የተነሡ ነፋሳትም ዊይይይይው፣ዊይይይይው ብለው አጨበጨቡ፡፡

ምድርም ተናገረች፣ እንዲህም አለች «እኔ እዞራለሁ፣ ቀንና ሌሊትን አፈራርቃለሁ፣ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉ እሰጣለሁ፤ አገልግሎቴን እንጂ እኔን ካልፈለጉኝ፤ ጥቅሜን ወስደው እኔን በኬሚካል እና በበካይ ጋዝ ከገደሉኝ ለምን እዞራለሁ፤ ዛፎቼን ቆርጠው ሳንባ ከነሱኝ ለምን እንከራተታለሁ?»

የፍጡራን አቤቱታ ሲያበቃ ሕፃኑ ቀጠለ

«እኔ ለፈጣሪ አንድ ጥያቄ አለኝ»

ከሰማይ የመጣውም ድምጽ «ተናገር» አለው፡፡

«አንተ የሕይወት መገኛ ነህ፤ ግን አንተ ትሞታለህ?» አለና ጠየቀ፡፡

በዚህ ጊዜ ሞት ደነገጠ፤ ነገሩ በእርሱ ላይ የተጠመጠመ መሰለውና የሁላገርሽን ነፍስ በሁለት እጁ እንደ ማቀፍ አደረጋት፡፡ ምንም እንኳን የሞት እቅፍ ባይሞቅ፡፡

«ደግሞስ» አለ ሕፃኑ «አባት እና እናታችሁን አክብሩ ብለሃል፤እኔ ስወለድ እናቴ ከሞተች ሕግህ እንዴት አድርጎ ይፈጸማል? እናትነትስ እንዴት ክብር ይሆናል? መው ለድኮ በዓለም ላይ ትልቁ ኃላፊነት ነው፡፡ ሰዎች ገንዘብ፣ ወርቅ፣ አልማዝ በኃላፊነት ሊቀበሉ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ሁሉ ግን ሰው ይበልጣቸዋል፡፡ ሰውን ያህል ፍጡር በኃላፊነት ተቀብሎ፤ ተሸክሞ፤ አሳድጎ፤ ከሚበሉት አካፍሎ፤ ተጠንቅቆ፤ የራስን ሕይወት አካፍሎ፤ መከራን ተቀብሎ ሰው ማድረግ የፈጣሪን ሥራ መሳተፍ ነው፡፡ ይህንን ኃላፊነት የተወጣች እናት መሸለም ሲገባት እንዴት ሞት ይታዘዝባት?

«እንዲያውም አንድ ሕይወት ለሰጠች ሁለት ይገባት ነበር፡፡ እርሷኮ ሠላሳ፣ ስድሳ፣ መቶ ያፈ ራች ዛፍ ናት፤ እንዴት ትቆረጣለች? የፍትሕ ሀገሯ የት ነው? የርትዕስ ማደርያዋ ወዴት አለ?

«ከዚህ በላይስ ፍቅር ወዴት ይገኛል? ሕይወት ለመስጠት ሲሉ ከመሞት፣ ራስን ለሌላ ሲሉ ከመሠዋት በላይስ ፍቅር የታለ? የፍቅር ዋጋውስ ይህ ነውን? ራሱ ፈጣሪስ ፍቅር አይደለምን? ታድያ ለዚህ ፍቅሩ ዋጋው ሞት መሆን አለበትን?

እነሆ ከሰማይ ድምፅ መጣ፡፡

«ሕይወት የምትሰጥ እናት ሕይወት እየሰጠች በወሊድ መሞት የለባትም፤ ለሕይወት ሞት፤ ለደግነትም ክፋት፣ ለጣፋጭም መራራ ሊከፈል አይገባም» አለ፡፡

ይህን ጊዜ ሞት የሁላገርሽን ነፍስ ወደ መሬት ለቀቃት፡፡ መላእክትም እልል አሉ፡፡ የመላእክትን ድምፅ ሰምተውም ለልቅሶ ተዘጋጅተው የነበሩ የመንደሯ ሴቶች አብረው እልል አሉ፡፡

«እናት ሕይወት ስትሰጥ ሕይወቷን እንድታጣ ያደረገ ባል፣ መንደርተኛ፣ ሐኪም፣ ሾፌር፣መድ ኃኒት ሻጭ፣ርዳታ ሰጭ፣አዋላጅ፣እስከ ሰባት ትውልድ ነፍሱ አትማርም» የሚል አዋጅም ታወጀ፡፡

ይህን ጊዜ በቤቱ የሕፃን ልቅሶ ተሰማ፤ የመንደሩም ልቅሶ በሁለት እልልታ ታጀበ፡፡ በሁላገርሽ ትንሣኤ እና በሕፃኑ መወለድ፡፡